## ራሱን ሲኖዶስ ብሎ የሚጠራው ሕገ ወጥ ቡድን በዋሽንግተን ዲሲ ሰሜን አሜሪካና በቶሮንቶ ካናዳ  ፈጽሟል የተባለውን ኢ-ቀኖናዊ ተግባር ለመመርመር የተደረገ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ስብሰባ

| | |
|---|---|
| - ጉባኤ የተካሔደው፡- | በአዲሱ የመንበረ ፓትርያርክ መሰብሰቢያ አዳራሽ |
| - የጉባኤው ዕለት፡- | ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም. |
| - ጉባኤው የተጀመረበት ሰዓት፡- | ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ |

### በስብሰባው ላይ የተገኙ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

1. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ<br>ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም<br>ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት<br>የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት------------ሰብሳቢ

2. ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ<br>የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ----------------------------------->>

3. ብፁዕ አቡነ  መርሐ ክርስቶስ<br>የመቀሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ----------------------------------->>

4. ብፁዕ አቡነ  ዘካርያስ<br>የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ------------------------>>

5. ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም<br>የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ------------------------------->>

6. ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ሊቀ ጳጳስ<br>የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የበላይ ኃላፊ----------------->>

7. ብፁዕ አቡነ  ገሪማ<br>የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣<br>የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊ፣<br>የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ቢሮ ዋና ጸሐፊና<br>የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ……………>>

8. ብፁዕ አቡነ  ኒቆዲሞስ<br>የወላይታና ዳውሮ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ………………………>>

9. ብፁዕ አቡነ  አትናቴዎስ<br>የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ----------------------------- >>

10. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ
የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ------------------------------ አባል

11. ብፁዕ አቡነ ቶማስ
የአዊ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ---------------------------------- >>

12. ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
በሰሜን ምዕራብ ሸዋ የሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ------------ >>

13. ብፁዕ አቡነ አረጋዊ ሊቀ ጳጳስ
የመንበረ ፀባዖት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል የበላይ ኃላፊ--------------- >>

14. ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ
የቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ሙዝየምና የትንሣኤ ዘጉባኤ
የኢሉባቦርና የጋምቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ----------------- >>

15. ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ --------------------------- >>

16. ብፁዕ አቡነ መልከ ጼደቅ
የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣
የከምባታ ሐዲያና ጉራጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ---------------- >>

17. ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ--------------------------------- >>

18. ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ
የምዕራብ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ----------------------------- >>

19. ብፁዕ አቡነ ኢሳይያስ
የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ---------------------------------- >>

20. ብፁዕ አቡነ ዮናስ
የአፋር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ------------------------------------ >>

21. ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ
የጅማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ------------------------------------- >>

22. ብፁዕ አቡነ እንድርያስ
የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ---------------------------- >>

23. ብፁዕ አቡነ ስምዖን
የመተከል ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ---------------------------------- >>

24. ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል
የከፋ ቦንጋ ቤንች ማጂ አህጉረ ስብከት ጳጳስ -------------------- >>

25. ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ
የደቡብ ትግራይ ማይጨው ሀገረ ስብከት ጳጳስ------------------ >>

26. ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል
በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ረዳት ጳጳስ…………………… አባል

27. ብፁዕ አቡነ ዳንኤል
የሰሜን፣ የምሥራቅና ምዕራብ አፍሪካ ሀገረ ስብከት ጳጳስ……….. >>

28. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ሽሬ ሀገረ ስብከት ጳጳስ--------------- >>

29. ብፁዕ አቡነ ያሬድ
የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ------------------------------ >>

30. ብፁዕ አቡነ ሔኖክ
የምዕራብ ወለጋና የአሶሳ አህጉረ ስብከት ጳጳስ----------------- >>

31. ብፁዕ አቡነ ቀሌምንጦስ
የምሥራቅ ሐረርጌና የሱማሌ አህጉረ ስብከት ጳጳስ------------- >>

32. ብፁዕ አቡነ እንባቆም
የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ------------------------------------ >>

33. ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ
የትግራይ ምሥራቃዊ ዞን አዲግራት ሀገረ ስብከት ጳጳስ------- >>

34. ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ
በመቀሌ የደብረ ሰላም ቅ/ሚካኤል ካቴድራልና
የከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማ ቅ/ፍሬምናጦስ
መንፈሳዊ ኮሌጅ ጳጳስ--------------------------------------------- >>

35. ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
የዋግ ሕምራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ --------------------------------- >>

36. ብፁዕ አቡነ ሰላማ
በክልል ትግራይ የአክሱምና ማዕከላዊ ዞን ሀገረ ስብከት ጳጳስ-- >>

37. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ
የነገሌ ቦረና ሀገረ ስብከት ጳጳስ------------------------------------- >>

38. ብፁዕ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ
የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ------------------------------ >>

39. ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል
የዋሽንግተን ዲሲና የአካባቢዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ -------------- >>

40. ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ሊቀ ጳጳስ
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና
የመ/ፓ/ቅ/ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ ------- የጉባኤው አባልና ጸሐፊ በመሆን በአንድነት ስብሰባን አድርገዋል።

## የስብሰባው አጀንዳ

፬ራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ይሡሩ ዘንድ ከተሠየሙ በኂላ፤

- ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በራሳቸው ፈቃድ ሥራውን ለቀው፣
- የፓትርያርክነቱን ሥልጣን አስረክበው፣
- ቤተ ክርስቲያናቸውን ከድተው፣
- ሀገር ጥለው የኮበለሉት አባ መርቆሬዎስ ከእናት ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ አስተዳደር መንበር ውጭ በሰው ሀገር ሁነው በሌላቸው ሥልጣን መጠቀምን ሽተው በውግዘት ከተለዩት ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋሽንግተን ዲሲ ሰሜን አሜሪካና ጥር 20 ቀን 1999 ዓ.ም. በካናዳ ቶሮንቶ የፈጸሙት ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያፋለሰ ሆኖ በመገኘቱ ይህኑ መሠረት በማድረግ ከየአቅጣጫው በቀረበው መግለጫና ሪፖርት ፍሬ ሐሳብ ተነጋግሮ ከሕገ ቤተ ክርስቲያኑና ከፍትሕ መንፈሳዊ ድንጋጌ አንጻር አስፈላጊውን ለመወሰን የተከፈተ ጉባኤ ነው ።

ቅዱስ ሲኖዶስ፤

1. የ፬ራተኛው ፓትርያርክ የታሪክ ማኅደር ዘግቦ ካቆየው የተዛባ የፓትርያርክነት ምርጫ አፈጻጸም ደረጃ ጀምሮ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እስከለቀቁበት ድረስ ያለውን ታሪክና፣

2. በብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት መሪነት ወደሰሜን አሜሪካ የተላከው የሰላም ልዑክ ያቀረበውን ዘገባ በስፋትና በጥልቀት ከመረመረ በኂላ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል ።

## መግለጫ

መላው ዓለም እንደሚገነዘበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓረፍተ ዘመኑ የተለያዩ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ችግሮች ቢፈታተኗትም መሠረቷ ክርስቶስ እንደ መሆኑ እስካሁን ድረስ በአንድነቷና በህልውናዋ ጸንታ ኖራለች፤ ወደፊትም ትኖራለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራሷን በራሷ ማስተዳደር ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሊቃውንት፣ በምእመናንና በካህናት እያስመረጠች ስትተዳደርና ስታስተዳድር ኑራለች፡፡

ይሁን እንጂ ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ1980 ዓ.ም. በግንቦት ወር መጨረሻ ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ሲለዩ፤ ወታደራዊው አስተዳደር ደርግ አባ መርቆሬዎስን ከሕገ ቤተ ክርስቲያን መመሪያ ውጭ ዐራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አድርጎ አስቀመጣቸው ፡፡

በመሠረቱ የትናንቱ አባ ዘሊባኖስ የዛሬው አባ መርቆሬዎስን ለኤጲስ ቆጶስነት ደረጃ ያደረሳቸው ችሎታና ብቃት ምን እንደነበረ ለሕዝበ ክርስቲያን ግልፅ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው ፡፡

በወታደራዊው ደርግ እንቅስቃሴ መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ‹‹ማኅበረ ካህናት›› በሚል ስያሜ ተነሣሥቶ ብዙ ካህናትን እያስተባበረ ክስና አቤቱታ በማቅረብ በቀድሞው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሕይወት ጉዳይና በዚያም ምክንያት በኢትዮጵያና በእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ለቆየው መልካም ግንኙነት መቋረጥ አስተዋፅዖ ላደረገው ወቅታዊ የግርግር ቡድን የዚያን ጊዜው አባ ዘሊባኖስ መሪ ተዋናይ ነበሩ ፤ ለኤጲስ ቆጶስነት ደረጃ ያሳጫቸውም ይኸው ነበር ፡፡

አባ መርቆሬዎስ መጀመሪያ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው የተመደቡበት ሀገረ ስብከት በኦጋዴን አካባቢ ጎዴ ሆኖ ሳለ በቤተ ክርስቲያን ሕግ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁጥር 158 የተደነገገውን በመጣስና በወቅቱም የብዙኃን ኢትዮጵያውያን ወገኖች ንጹሕ ደም በግፍ የፈሰሰበትን ቀይ ሽብርን በመቃወም ብርቱ አቋም የወሰዱትን የጎንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ እንድርያስን ያለ ሕግ በማሥነሣት አባ መርቆሬዎስ ከጎዴ ወደ ጎንደር የተዛወሩት በደርግ እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ተልዕኮ ከነበራቸው የወቅቱ ባለሥልጣኖች ጋር በመመሣጠር ሲሆን ይህም ድርጊት ራሱ ለፓትርያርክነት ሥልጣን ከመጀመሪያ አንሥቶ የነበራቸውን ምኞት ዕውን ለማድረግ የታቀደ ስልት ነበር ፡፡

አባ መርቆሬዎስ የደርግን አረመኔያዊ ፍላጎት ለማስፈጸም ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ከጎዴ ወደ ጎንደር ከተዛወሩ በኋላ ስንኳን ጳጳስ አንድ ክርስቲያን ሊፈጽመው የማይገባ አሳፋሪና አሳዛኝ ተግባር ሲፈጽሙ ቆይተዋል ፡፡

ይኸውም በጎንደር ሀገረ ስብከታቸው ከአንድ ክፍለ ሀገር በመለየት የሰሜን ጎንደር ወጣቶች እጅ እግራቸው እየታሰረ ከእነሕይወታቸው በገልባጭ መኪና እየተጫኑ ሊማሊሞ ገደል ሲወረወሩ እየሰሙና እያወቁ ለቀይ ሽብር እልቂት ድጋፍ ሰጥተዋል ፡፡ የእርሳቸው እጅ የተጨመረበትና በግፍ የፈሰሰውም የንጹሐን ደም እጅግ በርካታ ነበር፡፡

ፀረ-አብዮትና ፀረ-ደርግ አቋም አላቸው በመባል በግፍ እየተገደሉ በየቦታው ይጣሉ የነበሩ ክርስቲያኖች ጸሎተ ፍትሐት እንዳይደረግላቸው መመሪያን ሲሰጡ ቆይተዋል ። በኢትዮጵያ የታወቁ እንደነዋልድባ ያሉ ቀደምትና ታላላቅ ገዳማት ‹‹የጦር መሣሪያ ማከማቻ የፀረ አብዮት መሸሸጊያ ናቸው፤ መነኮሳቱም በቆባቸው ውስጥ ቦምብ ተሸክመው የሚሔዱ ስለሆነ መፈተሽ አለባቸው›› በማለት ገዳማቱም ሆኑ መናንያኑ የነበራቸው ከበሬታና ቅድስና እንዲጎድፍ ነቅፈው ለነቃፊ ከመስጠታቸው ባሻገር ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል ወደሳቸው የሚመጡትን ገዳማውያን የፀረ አብዮት ተባባሪዎች እያሉ ሲያባርሩዋቸው፤ በጊዜው ለነበረው እጅግ የከፋ ረኃብና ቸነፈር መቋቋሚያ እንዲሆን ለገዳሙ ይላክ የነበረውን ልዩ ልዩ ርዳታ በማስመለስ ራሳቸው ወደፈለጉት አቅጣጫ እንዲውል ሲያደርጉ ቆይተዋል ።

ክርስቲያኖች ከሃይማኖታቸውና ከመንፈሳዊ ሥርዓታቸው ውጭ በጐንደር ሀገረ ስብከት በአጽዋማት ጊዜ ሥጋ እንዲበሉ በኢሠፓ ካድሬዎች ሲገደዱ የተቃወሙ ሊቃውንትና መምህራን በአደባባይ አይቀጡ ቅጣት እየተቀጡ ፍዳ ሲቀበሉ፤ የቆሎ ተማሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እየታፈኑ ወደ ጦርነት ሲወሰዱ ከመደገፍና ከማስተባበር በቀር በመቃወም ያደረጉት እንቅስቃሴ ፈጽሞ አልነበረም ።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው አባ መርቆሬዎስን ለፓትርያርክ መንበር ዕጩ አድርገው ካቀረቡአቸው ነጥቦች ዋነኛዎቹ የወቅቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴአቸውና ጥረታቸው ሁሉ የደርግን ዓላማ በማራመድና መመሪዎችን በማስፈጸም ላይ ያተኮረ ሆኖ መቆየቱ፤ በዚያውም ለብሔራዊ ሸንጎ መደበኛ አባል ሆነው መመረጣቸው ነው ። ከደርግ ጋር በሥልጣን፣ በጥቅምና ፖለቲካ የተሳሰሩባቸው የቃል ኪዳን ሰንሰለቶች በቤተ ክርስቲያን ሕግ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ቁ 199 የተደነገገው ተጥሶ በኢሰፓውያን ሿሚነት የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ሊያስጨብጧቸው ችለዋል ። የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣ ካህናትና ምእመናን በወቅቱ ይህን ሕገ ወጥ አፈጻጸም የተቃወሙትና ያልተቀበሉት ቢሆንም ከቅሬታና ከኀዘን አልፈው ሌላ ርምጃ ሊወስዱ ጊዜ አልፈቀደላቸውም ነበር ።

የቀድሞው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካረፉ በኋላ አባ መርቆሬዎስ ባቋራጭ ገብተው ፓትርያርክ የተባሉት በወቅቱ መላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተሰብስበው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መመሪያ መሠረት ተገቢውን አባት ለማስመረጥና በተገቢው መንበር ላይ ለማስቀመጥ አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቀው ምርጫውን በመጀመር ላይ እንዳሉ በደርግና በሃይማኖት ሚኒስትር ተጽእኖ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ እንዲበተን ተደርጎ ነው ።

አባ መርቆሬዎስን ለማስመረጥ በወቅቱ የተዘጋጀውን ልዩ መስፈርት ያቀነባበሩት የደርግ ኢሰፓ የፖለቲካ ቢሮ መሪ አባላት የነበሩ ከሃይማኖት ሚኒስቴር፣ ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትና ከሌሎችም ድርጅቶች በልዩ ልዩ ሥልጣን ላይ የነበሩ ደጋፊዎቻቸው ተሰባስበው እንደነበር ግልፅ ነው ። ምርጫ ተካሔደ የተባለውም ለሴራው ሽፋን ያህል ከየሀገረ ስብከቱ እንዲመጡ የተደረጉ መራጮች አባ መርቆሬዎስን ብቻ እንዲመርጡ ከየአካባቢአቸው ኢሠፓ ጽ/ቤት ልዩ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው አዲስ አበባ ከደረሱም በኋላ ምርጫው እስኪፈጸም (ድምፅ እስከሚሰጥ) ድረስ በአንድ ቦታ ተወስነው

ከሰው ሳይገናኙ እንዲቆዩ በማድረግ ነበር ፡፡ በወቅቱ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትም ቤተ ክርስቲያን እንዳትጎዳ በትዕግሥት አልፈውታል ፡፡

ተወዳደሩ ለማሰኘት አብረው እንዲቀርቡ ለተደረጉት ሊቃነ ጳጳሳት የሚሰጥ ድምፅ ቢኖርም ደርግ ካሰበው ውጭ እንዳይፈጸም የአባ መርቆሬዎስ ደጋፊዎች ከነበሩ ባለሥልጣኖች ጋር በመመሣጠር የራሱን ድምፅ ቆጣሪዎችና አስቆጣሪዎች በመመደብ በድርጅታዊ አሠራር የተፈጸመ ነበር ፡፡

አባ መርቆሬዎስ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን የያዙት ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ከመሆኑም በላይ ይህኑ ኢ-ሕጋዊ ሥልጣን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን እየተከታተሉና እየገመገሙ ሁኔታውን በትዝብትና በኀዘን እየተመለከቱ ጊዜውን ሲጠብቁ የቆዩት ሕዝበ ክርስቲያንና ካህናት በመላ ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር ተነሣሥተው ተቃውሞአቸውን አስተጋቡ፤

በዚሁ መሠረት ምእመናንና ካህናት፣ ሊቃውንትና መምህራን ተሰባስበውና ተወያይተው አባ መርቆሬዎስ ያለ አግባብ ከያዙት ሥልጣን እንዲነሡ የተቃውሞ ውሳኔ አስተላልፈዋል፤ የአመራር ይዞታቸውንና ድርጊታቸውንም አውግዘዋል ፡፡

ተቃውሞውና እንቅስቃሴው በዚሁ ሁኔታ በመቀጠል ላይ እንዳለ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ተቆጣጠረ፤ ከዚህም በመቀጠል ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ካህናትና ምእመናን በአባ መርቆሬዎስ ላይ የሚያደርጉት ተቃውሞ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች አስተጋባ ፡፡

አባ መርቆሬዎስ በቤተ ክርስቲያን አመራርና በሀገሪቱ ያደረሱት ጥፋት በመገናኛ ብዙኃን በተከታታይ በስፋት ተገለጠ፤ ተነገረ፤ የሽግግሩ መንግሥት በሰጠው የዲሞክራሲ መብት መሠረት ቀደም ሲል በልዩ ልዩ ጊዜያትና ስብሰባዎች ተቃውሞአቸውን ያስተጋቡ የነበሩት በአዲስ አበባና በአካባቢዋ እንዲሁም በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙ ካህናትና ምእመናን ተቃውሞአቸውን በስፋትና በጥልቀት በሰላማዊ ሠልፍ ገለጡ ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ራሳቸው አባ መርቆሬዎስ በመላ ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት የሚገኙት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በወርኃ ነሐሴ በጾመ ፍልሰታ ለማርያም እንዲሰበሰቡ ጥሪ አስተላለፉ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሰበሰበም ‹‹እዚህ ቅዱስ መንበር ላይ የተቀመጥኩት በማን እንደሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፤ ሆኖም በሥራው ብዛትና ክብደት ምክንያት ሕመም ካደረብኝ ብዙ ጊዜ ቆይቷል ፤ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሥራ እንዳይበደል ቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነቱን ተረክቦ እንዲሠራ እንድታደርጉ›› በማለት ሥልጣናቸውን ለቅዱስ ሲኖዶስ አስረክበዋል ፡፡

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ.ም. ባደረገው ምልዐተ ጉባኤ የቅዱስ ፓትርያርኩን ጤንነት ለመጠበቅና የቤተ ክርስቲያናችንም ሥራ እንዳይበደል ፓትርያርኩ ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል የቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር ቅዱስ ሲኖዶሱ ተረክቦ በተገቢው ሁኔታ እንዲካሔድ ማድረግ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት ባቀረቡት አቤቱታ መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር ቅዱስ ሲኖዶስ ተረክቦ እንዲሠራ፤ አባ መርቆሬዎስም በጠበልና በሕክምና እንዲረዱ ቅዱስ ሲኖዶስ በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ወስኗል ፡፡

ከዚህም ጋር አባ መርቆሬዎስ ለጤንነታቸውም ሆነ ለመንፈሳዊው ሕይወታቸው ከሌሎች ገዳማት ይልቅ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ለጠበልም ሆነ ለሕክምና አመቺ ሆኖ በመገኘቱ በተጠቀሰው ገዳም በጸሎት ተወስነው እንዲቀመጡ፤ በገዳሙም የሚኖሩበት የተሻለ ቤት ተመርጦ እንዲሰጣቸው፤ ደመወዝና መኪናም እንዲመደብላቸው በመወሰን አስፈላጊውን እንክብካቤ አድርጎላቸዋል ።

አባ መርቆሬዎስም ምልዓተ ጉባኤው ያሳለፈውን ውሳኔ በደስታ ተቀብለው ስለተደረገላቸው ድጋፍና እንክብካቤ ሁሉ ምስጋናን አቅርበዋል።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱን አጠቃላይ ኃላፊነት ተረክቦ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ለመያዝ ከፍተኛ ጉጉት በነበራቸው በአባ ዜና ማርቆስ የመጀመሪያ ሰብሳቢነት ሊቃነ ጳጳሳትን መርጦ ሥራውን በማካሔድ ስለተተኪው አምስተኛ ፓትርያርክ ምርጫ አፈጻጸም በጥልቀትና በስፋት ሲያጠና ቆይቶ ግንቦት 5 ቀን 1984 ዓ.ም. ባደረገው ምልዓተ ጉባኤ፤ መንበር ያለ መምህር ፤ ሲኖዶስ ያለ ፓትርያርክ መኖር ስለማይገባው የአምስተኛው ፓትርያርክ ምርጫ ሰኔ 28 ቀን 1984 ዓ.ም. እንዲፈጸም የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፤

በውሳኔውም መሠረት ከመላ ኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት ታላላቅ ገዳማትና አድባራት የተወከሉ፤

- የካህናት፣
- የምእመናንና
- የሰንበት ትምህርት ቤቶች ተወካዮች በተገኙበት አምስት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በዕጩነት ቀርበዋል፤ ከቀረቡት ዕጩ ተወዳዳሪዎችም መካከል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ባላቸው ሁለንተናዊ ብቃት ከፍተኛውን ድምፅ በማግኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምስተኛው ፓትርያርክ ሆነው ተመርጠዋል ።

ሥርዓተ ሢመቱም፤

- የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣
- የገዳማት አበ ምኔቶች
- የአድባራት አስተዳዳሪዎች
- መላው ካህናትና ምእመናን
- የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶች

የኦሬንታልና የኢስተርን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና የሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች በተገኙበት ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ.ም. ቀኖና ቤተ

ክርስቲያን በሚያዘው ድንጋጌ መሠረት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል ።

ይህን ሁሉ ዝርዝር ሁኔታ በተመለከተም አፈጻጸሙ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት የተፈጸመ መሆኑ በወቅቱ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን በተደጋጋሚ ተገልጿል ።

የአባ መርቆሬዎስ ከፓትርያርክነት ሥልጣን መውረድና የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምስተኛ ፓትርያርክ ሆኖ መሾም ዝርዝር ሁኔታ ይህ ሁኖ ሳለ፤ አባ መርቆሬዎስ ግን ማንም ሳያሳድዳቸው በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 156 እና 158 የተደነገገውን በመጣስ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከድተውና የቤተ ክርስቲያኒቱን መኪና ይዘው ሀገር ጥለው ወጡ።

አባ መርቆሬዎስም ሆኑ ሌሎች ተከታዮቻቸው ማለትም፤

1. አባ ዜና ማርቆስ፣
2. አባ ኤልያስ፣
3. አባ መልከ ጼዴቅ
4. አባ ጎርጎርዮስ፣

ከዚህ በላይ ስማቸው የተጠቀሰው በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 156 ረሰጠብ 11 የተገለፀውን ‹‹አንድ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ጳጳስ መንበሩንና ሀገረ ስብከቱን ትቶ ወደ ሌላ ሀገረ ስብከት ይሔድ ዘንድ አይገባውም›› የሚለውን ሕገ ሲኖዶስ ጥሰው፣ ሀገር ጥለው፤ ለማገልገል ቃል የገቡላትን ቤተ ክርስቲያን ክደው ከሀገር ከወጡ በኋላ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በሚቃረን መልኩ ሕገ ወጥ ተግባርን ሲፈጽሙ በመገኘታቸው፤

ሀ/ ጳጉሜን 2 ቀን 1984 ዓ.ም.

ለ/ መስከረም 15 ቀን 1985 ዓ.ም. ቅዱስ ሲኖዶስ ባደረገው ምልዓተ ጉባኤ ከማናቸውም የክህነት አገልግሎትና የጵጵስና ሥልጣናቸው ታግደዋል የጵጵስና መጠሪያ ስማቸውም ተነሥቷል በማለት ውሳኔን አሳልፎአል ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በሀገሩ ኢትዮጵያ፤ በመንበሩ እያለ፤ በተለያየ ምክንያት ከሀገሩ ወጥቶ በሰው ሀገር የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን ለማደናገርና ለመከፋፈል ይልቁንም ለሁለት ሺህ ዘመናት በአንድነቷ ጸንታ የኖረችውን ሐዋርያዊት፣ ታሪካዊት፣ ብሔራዊትና ጥንታዊት የሆነችዋን አንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈልና ለማዳከም አቅደው ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ›› በሚል አጠራር ራሳቸውን ሰይመው፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጥሰው ንጹሐኑን ሕዝበ ክርስቲያን ለ15 ዓመታት ያህል ሲያደናግሩ፣ ሲከፋፍሉና ሲያተራምሱ መኖራቸውን መላው ዓለም የሚያውቀው ጉዳይ ነው ።

ግለሰቦቹ ከሀገር ከወጡበት፣ ከቤተ ክርስቲያናቸው ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ ንስሐ ገብተው ወደ እናት ሀገራቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው የሰላም ጥሪውን ሲያስተላለፍ ቆይቷል፤ ከዚህም በላይ በቅርቡ በሊቃነ ጳጳሳት

የተመራ የሰላም ልዑክ ካሉበት ቦታ ድረስ ተልኮ የቅዱስ ሲኖዶሱን የሰላም መልእክት ለማድረስና በግንባርም ተገናኝቶ ለመወያየት፤ ብሎም ወደ ሀገራቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው የሚመለሱበትን መንገድ ለማመቻቸት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፤ ልዑኩ ያደረገውም ጥረት ሁሉም ሰው እንዲያውቀው በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ መገናኛዎች መገለፁ ይታወሳል ፡፡

ይሁን እንጂ አባ መርቆሬዎስና ሌሎቹም ቅዱስ ሲኖዶስ ያደረገውን የአንድነትና የሰላም ጥሪ ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም፤ ቅዱስ ሲኖዶስ እነሱ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመለሱ ያደረገው ጥረት ይህን ያህል ሆኖ ሳለ፤ ይባስ ብለው፤ አባ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን ለቅዱስ ሲኖዶስ አስረክበው የተሰናበቱ ሲሆኑ፤ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው የጵጵስና ሥልጣናቸው ከነመዓርግ ስማቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ከታገደ በኋላ ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም የሚያበቃ ሲኖዶሳዊ ሥልጣን ሳይኖራቸው የሐዋርያትን ሲኖዶስ በመጣስ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ጥር 13 ቀን 1999 ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ ሰሜን አሜሪካና እንዲሁም ጥር 20 ቀን 1999 ዓ.ም. በቶሮንቶ ካናዳ የፈጸሙት ሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያፋለሰ፣ በ381 ዓ.ም. ሁለተኛው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ያሳለፈውን ውሳኔ የጣሰ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርጊቱን አጥብቃ ታወግዘዋለች፤ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የሚገኙ ተከታዮቿ ምእመናንም የተፈጸመው ክህደት የተመላበት ተግባር ታሪኳን የሚያጎድፍ፣ አንድነቷን የሚከፋፍል፣ ልዕልናዋን የሚፈታተን ኢ-ሕጋዊ ድርጊት መሆኑን አውቀውና በጥልቀት ተገንዝበው በያሉበት ቦታ አጠብቀው እንዲቃወሙትም በከፍተኛ ድምፅ ጥሪዋን ታቀርባለች ፡፡

- ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የአባ መርቆሬዎስ ወደ ፓትርያርክነት ሥልጣን መምጣትና ከሥልጣን የመውረዳቸው ታሪክ በአጭሩ ተመዝግቧል ፡፡

- አባ መርቆሬዎስ ከፍትሕ መንፈሳዊ ድንጋጌ ውጭ ሥልጣናቸውን በራሳቸው ፈቃድ ለቀው ከሀገር ከወጡ በኋላ ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሠየም ሥልጣኑም ሆነ መብቱ ሳይኖራቸው በተወገዙት ተከታተዮቻቸው ግፊትና አጃቢነት ሀገሪቱንና ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚከፋፍል ታላቅ ክህደት ፈጽመው በመገኘታቸው የፈጸሙት ኢ-ቀኖናዊ ተግባር ቅዱስ ሲኖዶሱን በእጅጉ አሳዝኗል ፡፡

ከዚህ ግንዛቤ በመነሣት ምልዓተ ጉባኤው ቀጥሎ ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል ፡፡

# ውሳኔ

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ‹‹ ደቂቅየ !! ዛቲ ሰዓት ደኃሪት ይእቲ ወበከመ ሰማዕክሙ ከመ ይመጽእ ሐሳዊ መሢሕ ወይእዜኒ ኮኑ ብዙኃን ሐሣውያነ መሢሕ ወበዝንቱ አእመርነ ከመ ድኃሪት ሰዓት ይእቲ እስመ እምኔነ ወጽኡ አለ ኢኮኑ እምኔነ ወሶበሰ እምኔነ እሙንቱ እምነበሩ ምስሌነ››

‹ልጆቼ ይህቺ የመጨረሻ ሰዓት ናት እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ ሐሳዊ መሢሕ እንደሚመጣ እንደሰማችሁ ሁሉ አነሆ በአሁኑ ሰዓትም ብዙዎቹ ሐሣውያነ መሢሕ ሆነዋል፤ በዚህም የመጨረሻዋ ሰዓት እንደሆነች፣ እንደደረሰች አወቅን ተረዳን ከእኛ ያልሆኑ ከእኛ ዘንድ ወጥተዋልና ከእኛ ጋርማ ቢሆኑ ኑሮ ከእኛ ጋር በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉም ከእኛ ዘንድ እንዳልሆኑ ይታወቁ› ብሎ እንደገለፀው ሁሉ /1ኛ ዮሐ. 2፣ 18-19/

- አባ መርቆሬዎስ በራሳቸው ጥያቄ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን አስረክበው፤ ሀገራቸውን ጥለው፤ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከድተው በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 105 ድስቅ 34 ‹‹ኤጲስ ቆጶስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾም ዘንድ እናዛችኋለን፤ የችግር ዘመን ቢሆን ግን በሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾም፤ በአንድ ኤጲስ ቆጶስ ግን ሊሾምላችሁ አይገባም የሁለትና የሦስት ምስክርነት የጸና ይሆናልና፤ ረሰጣ 58 አንድ ኤጲስ ቆጶስ ብቻውን የሾመ ከሆነ ይለይ /ይሻር/›› የሚለውን በመተላለፍ፤

- በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 194 ረሰጣ 34 ረሰጠጅ 24 ‹‹ባለሀገረ ስብከቱ ሳይፈቅድለት ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ካህንን የሾመ ቢኖር ይሻር›› በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 206 ኒቅያ 24 ‹‹ኤጲስ ቆጶሳት ከሀገረ ስብከታቸው ወደ ሌላ ሀገር ቢሔዱ ከስድስት ወር የበለጠ አይኑሩ፤ ችግር ሳይገጥማቸው፣ ሊቀ ጳጳሳቱም ሳይፈቅድላቸው ከዚህ የበለጠ ቢኖሩ ወይም ሀገረ ስብከታቸውን ትተው በሌላው ሀገር በዓለ ትንሣኤን ቢያከብሩ ከሹመታቸው ይሻሩ›› የሚለውን ድንጋጌ በመጣስ፤

- በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 ቁጥር 138 ‹‹ከበጎች የተለየህ ብትሆን ጠላታቸው አንተ ነህ፤ የእግዚአብሔርም ባላጋራው ነህ፤ እግዚአብሔር ጠባቂ የሆናቸውን በጎች የምታጠፋ አንተ ነህ›› የሚለውን የሐዋርያት ሲኖዶስና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመግሠሥ፤

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ሲኖዶስ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2እና 3 እንደተደነገገው ‹‹ከሥልጣኑ የተገለለ ፓትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል፤ በገዳም አልቀመጥም፤ በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ግን ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ይለያል›› የሚለውን ድንጋጌ በመተላለፍ አባ መርቆሬዎስ የሐዋርያትን ሲኖዶስ፤ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን አፍርሰው ተገኝተዋል ፡፡

ስለዚህ

1. አባ መርቆሬዎስ በራሳቸው ፍላጎትና ጥያቄ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ለቅዱስ ሲኖዶስ ከማስረከባቸው የተነሣ የፓትርያርክነት ሥልጣን እንደሌላቸው እያወቁ ተወግዘው ከተለዩት፤

   ሀ/ አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ
   ለ/ አባ ዜና በጎ ሰው
   ሐ/ አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ
   መ/ አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደ ጋር በመሆን ሁሎችም በሌላቸው ሥልጣን ኤጲስ ቆጶሳትን ሹመናል ብለው በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመዋሸታቸውና በመዳፈራቸው፤

2. ለሁለት ሺህ ዘመናት ያህል በአንድነቷ ጸንታ የኖረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሆን ብለው ለመገነጣጠል አቅደውና አስበው ሕገ ወጥ ሲኖዶስ በማቋቋም በአሜሪካና በሌሎችም አህጉር የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን በማታለል የክህደትና የመናፍቅ ተግባር በመፈጸማቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቷቸዋል፤

   ሀ/ ሥልጣነ ክህነታቸውና የማዕርግ ስማቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ የተነሣ ስለሆነ ከዛሬ ጀምሮ አባ ዘሊባኖስ ፋንታ ተብለው በቀድሞ ስማቸው እንዲጠሩ፤

   ለ/ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አገልግሎት ዙሪያም በሕይወትም ሆነ በሞት ማናቸውንም መንፈሳዊውን አገልግሎት እንዳያገኙ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቷቸዋል ፡፡

3. ከሥልጣን በወረዱት በአባ ዘሊባኖስ ፋንታ በሚመራው ሕገ ወጥ የተሐድሶ መናፍቃን ቡድን ተሾመዋል የተባሉት ኤጲስ ቆጶሳት ተብየዎች የሐሰት ኤጲስ ቆጶሳትም ቤተ ክርስቲያናቸውን ጥለውና ክደው የሔዱ ከመሆናቸውም በላይ ለከፍተኛው የቤተ ክርስቲያን ማዕርግ የማያበቃ ነውርና ነቀፋ ያለባቸው፤ ሢመታቸውም ከሐዋርያት ሲኖዶስና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በመሆኑ ይህ ውሳኔ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ከዲቁና እስከ ቅስና ያለው ሥልጣነ ክህነታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ የተገፈፈና የተወገዘ ነው፤ ቤተ ክርስቲያናችንም አውግዛ ለይታቸዋለች፤ እያንዳንዳቸውም አባ ተብለው እንዲጠሩ ተወስኗል፤ አሁንም ተቀበሉት የተባለውን የሐሰት ሹመት ቤተ ክርስቲያናችን አልተቀበለችውም፤ ቅዱስ ሲኖዶስም አውግዞታል፤ በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዙሪያም በሕይወትም ሆነ በሞት ማናቸውንም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳያገኙ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ከቤተ ክርስቲያን ለይቷቸዋል ፡፡

4. እንዲሁም ‹‹በክርስቶስ ትምህርት ጸንቶ የማይኖርና ከእርሱም ርቆ የሚሔድ እግዚአብሔር ከርሱ ጋር የለም፤ … ይህንም ትምህርት ሳይዝ ማንም ወደናንተ ቢመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ምክንያቱም ሰላምታ የሚሰጠው ሰው ሁሉ የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና›› /2ኛ ዮሐ. ም.1፤ 9-11/ በሚለው መሠረት በሀገር፣ ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም የምትገኙ የጥንታዊቷና የታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፤

- ሊቃነ ጳጳሳት
- ጳጳሳት፣
- ቆሞሳት ፣
- ቀሳውስት፣
- ዲያቆናትና መዘምራን፣
- ምእመናንና ምእመናት በሙሉ በአባ ዘሊባኖስ ፋንታ መሪነት የተሰባሰቡትን የዘመናችን የፀረ ማርያምና የተሐድሶ መናፍቃን ስብስቦች የሚያስተላልፉትን ከንቱ ስብከት እንዳታዳምጡ፣ ትምህርታቸውንም እንዳትቀበሉ፣ ኢ-ቀኖናዊ ሥርዓታቸውን እንዳትከተሉ፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ከእነርሱ ጋር እንዳትሳተፉ፤ ወደ ቤታችሁም እንዳታስገቡ በማዕድ ተሳትፎም ኅብረት እንዳይኖራችሁ፤ የእናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ አውግዟል ።

5. ማናቸውም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተቋም በሕግ የተረጋገጠ የራሱ መለያ የሆነ፤ ስያሜ አለው፤ አንዱ የሌላውን፤ ሌላው የአንዱን መለያ ስም በፍላጎት በመንጠቅ ሊጠራበትና ሊገለገልበት እንደማይችል በዓለም አቀፍ ሕግ የተከለከለ ነው፤ ሕጋዊው አሠራር ይህ ሁኖ ሳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የምትጠራበትን ስም መጠቀም የሌለባቸው ስለሆነ ሀገርና ቤተ ክርስቲያንን ከድተው ወደ አሜሪካ የኮበለሉ ግለሰቦች በጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያ ስም ሊጠቀሙና ሊጠሩበት እንደማይችሉ ታውቆ አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲመሠረትባቸው ተወስኗል፤

6. ሀ/ <u>አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህን በተመለከተ</u>

ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ከውጪ ጠላቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከውስጥም ጠላቶች ጋር ትታገል እንደነበር ታሪክ በሰፊው ይገልፃል ፡

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን አስተምራ፣ ለከፍተኛ ደረጃ አብቅታ፤ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት ሰጥታ የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ዲን የነበሩት የቀድሞው አባ መልከጼዴቅ የዛሬው አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት፣ ዕሩያን በአካል የሚለውን የኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ትምህርት በማዛነፍ፡-

- ‹‹መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም፣ ዝርው ነው››
- በንጽሕተ ንጹሐን፣ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ላይ ያላቸው እምነትና ትምህርትም ከኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነት ውጪ ሆኖ

በመገኘቱ የበተኑት ጽሑፍ በሊቃውንት ጉባኤ ተመርምሮ ስሕተታቸው እውነት ሆኖ ስለተገኘ የበተኑትን ጽሑፍ እንዲያርሙ፣ ለፈጸሙትም የእምነት ሕጸጽ ተጸጽተው ይቅርታ እንዲጠይቁና የጽሑፍ ማስተባበያ በጋዜጣና በመጽሔት እንዲያስተባብሉ ከቅዱስ ሲኖዶስ ሐምሌ 11 ቀን 1984 ዓ.ም. በቁጥር 321/199/84 ተጽፎላቸው ሳለ መልስ ሳይሰጡ አገር ጥለው፣ ቤተ ክርስቲያንን ክደው ኮበለሉ ።

ከሀገር ከወጡም በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ከመዝለፍ፣ አንድነቷን ከመፈታተን ያልተቆጠቡ በመሆናቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ጳጉሜን 2 ቀን 1984 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ፤

- አባ መልከጼዴቅ ስህተታቸውን አውቀው፤ ንስሐ ገብተው እስኪመለሱ ከማናቸውም የክህነት አገልግሎትና ከጵጵስና ሥልጣናቸው ታግደዋል፤
- ምሥጢረ ሥላሴን  በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያናችን እምነት ውጪ ‹‹መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም›› በማለታቸው፤
- በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የተዛባ እምነትና ትምህርት በማስተማራቸው በጋዜጦችና በመጽሔቶች በአስቸኳይ እንዲወጣና ሕዝበ ክርስቲያኑ እንዲያውቀው በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አስተላልፈዷል፡፡

አባ ሀብተ ማርያም ይባስ ብለው በአሁኑ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በማፋለስ፣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በመፈታተን ላይ የሚገኘውን ሕገ ወጥ ቡድን በግንባር ቀደምትነት በማንቀሳቀስ ‹‹ቅዳሴ ማርያም መቀደስ የለበትም፣ ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ሥዕል፣ ተአምረ ማርያም፣ አመክንዮ ዘሐዋርያት መነበብ የለበትም ቅዳሴም ቢሆን በፒያኖ ታጅቦ መቀደስ አለበት›› በማለት እንደ ጥንቱ የክህደት አባታቸው አርዮስ ጽሑፍ በመበተን ላይ ስለሚገኙ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ተወግዘዋል፤ ምእመናንም ከእሳቸውና ከመሰሎቻቸው ጋር ምንም ዓይነት ኅብረትና ተሳትፎ እንዳያደርጉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ አውግዟል ።

## ለ/ አባ ዜና በኀ ሰውን በተመለከተ

አባ ዜና በኀ ሰው በነበራቸው ከፍተኛ ፓትርያርክ የመሆን የሥልጣን ጉጉት አባ መርቆሬዎስ አመመኝ ብለው ሥልጣኑን ለቅዱስ ሲኖዶስ ሲያስረክቡ ሲኖዶሱን እንኳ ሳያማክሩ ወዲያውኑ የሰብሳቢነቱን ሥራ በሥልጣናቸው በመያዝ አምስተኛ ፓትርያርክ እንዲመረጥ ከወሰኑ በኋላ ይጠብቁት የነበረውን የፓትርያርክነት ሥልጣን ማግኘቱ ይቅርና ለውድድር እንኳ ሳይበቁ፤ በመቅረታቸው በመጨረሻም በማያወላውል ሁኔታ ሥልጣኑ እግዚአብሔር ለፈቀደላቸውና ቅዱስ ሲኖዶስ ለመረጣቸው አባት ሲሰጥ አኩርፈው ከሀገር ወጡ፣ ከወጡም በኋላ ቤተ ክርስቲያኗን ለመከፋፈል ብዙ ሙከራ ሲያደርጉ በመቆየታቸውና የቅዱስ ሲኖዶስንም ሕግ በመተላለፋቸው ከአሁን በፊት ከጵጵስና ሥልጣን ታግደው የጵጵስና ስማቸውም ተነሥቶ ነበር፡፡ ሆኖም በፈጸሙት ጥፋት ንስሐ ገብተውና ተጸጽተው በመመለስ ፈንታ ጭራሽኑ በሌላቸው ሥልጣነ ጵጵስና ከሕገ ወጡ ቡድን ጋር በመሆን የቤተ ክርስቲያኗን

አንድነት ለማናጋት በሕገ ወጥነት በተፈጸመው ሹመት ላይ ተባባሪ በመሆናቸው ለሁለተኛ ጊዜ ተወግዘዋል፤ እንዲሁም በሕይወትም ሆነ በሞት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቷቸዋል ።

## ሐ/ አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬን በተመለከተ

አባ ገብረ እግዚአብሔር ጸጋዬ አባ መርቆሬዎስ ሥልጣኑን ሲያስረክቡ በነበሩበት በጅቡቲ ሀገረ ስብከታቸው ሆነው በሰሙ ጊዜ በሲኖዶስ ውሳኔ የተስማሙ፣ አምስተኛው ፓትርያርክ በተሾሙ ጊዜም ደስታቸውን በፋክስ የገለፁ ሆኖ ሳለ፤ ከብዙ ወራት በኋላ ቤተ ክርስቲያኗን ክደው ሊኮበልሉ ችለዋል፤ እኒህ ሰው ከዚህ ቡድን ጋር በመሆን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማፍረስ፣ ምእመናንንም ለመከፋፈል ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ጵጵስናቸው ታግዶ ነበር፤ የጵጵስና ስማቸውም ተነሥቶ ነበር፤ ሆኖም ከመመለስ ይልቅ በጥፋቱ መቀጠልን መርጠው ከጥፋት ቡድኑ ጋር ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈርስ ተግባር ሲፈጽሙ የተገኙ በመሆናቸው ለሁለተኛ ጊዜ ተወግዘዋል፤ እንዲሁም በሕይወትም ሆነ በሞት የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቷቸዋል ።

## መ/ አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደን በተመለከተ

አባ ኃይለ ኢየሱስ ከበደ እንደሌሎቹ የሲኖዶስ አባላት በአባ መርቆሬዎስ ሥልጣን መልቀቅ የተስማሙና የአምስተኛው ፓትርያርክ ምርጫም እንዲካሔድ ድጋፍ የሰጡ ሲሆን፣ ምርጫው ከተከናወነ በኋላ ፀራ ለጽድቅ በመሆን ቤተ ክርስቲያንን የከዱ ሰው ናቸው፤ ይህም በመሆኑ በፈጸሙት የክህደት ተግባር የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማፍረስና ምእመናንን ለመከፋፈል ሲንቀሳቀሱና እንዲሁም ሕገ ሲኖዶስን ተላልፈው ስለተገኙ ጵጵስናቸውና የጵጵስና ስማቸው ተነሥቶ እንደነበር ይታወሳል፤ ይህ በዚህ እንዳለ በሌላቸው ሥልጣን እንደሌሎቹ የቡድኑ አባላት በሕገ ወጥ ሁኔታ የሕገ ወጡ ሹመት ተባባሪ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን በመከፋፈል ኢ-ቀኖናዊ ተግባር ሲፈጽሙ በመገኘታቸው ለሁለተኛ ጊዜ ተወግዘዋል፤ እንዲሁም በሕይወትም ሆነ በሞት የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይፈጸምላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቷቸዋል ።

ከዚህ ላይ ሁሉም ሊያውቀውና ሊገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር እነዚህ የጥፋት መልእክተኞች አባ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን ባስረከቡበት ጊዜ ከነበሩት መላው ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተለይተው የኮበለሉበት ምክንያት ምንድን ነበር? የሚለውን እውነታ ማየቱ የሰዎቹን ማንነት ይበልጥ በጉልህ ለመረዳት ያስችላል ።

እንደሚታወቀው በወቅቱ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ያስተዳድሩ በነበረበት ወቅት ለአባ ዜና ማርቆስ እንደራሴነቱን፣ ለአባ መልከጼዴቅ የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ዲንነቱን፣ ለአባ ጎርጎርዮስ ልዩ ጸሐፊነቱን ተከፋፍለው መያዛቸው ማንነታቸውን በጉልህ ያሳያል ።

እነዚህ ግለሰቦች የነበራቸው ፍላጎት ሥልጣናቸውን በማስጠበቁ ላይ እንጂ የአባ መርቆሬዎስ ከሥልጣን መነሣት ጉዳያቸው አልነበረም፤ ይህንም ያደረጉበት ምክንያት

ሰዎቹ አባ ዜና ማርቆስን በፓትርያርክነት አስቀምጠው ሥልጣናቸውን የማስቀጠል ሕልሙ ስለነበራቸው ነው፤ ለዚህም ነበር እስከ አምስተኛው ፓትርያርክ ምርጫ ጊዜ አብረው የተጓዙት፤ የአምስተኛው ፓትርያርክ ምርጫ ከተከናወነ በኋላ ግን የነበራቸው ራእይ ግቡን ስላልመታ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንደሚባለው ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን ክደው በመውጣት ባለና በሌለ አቅማቸው ተረባርበው ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል በሥልጣን ጥመኝነት እኩይ መንፈስ ተነሣስተው ሕዝቡን ሲያተራምሱ ቆይተዋል ።

ይሁንና ቅዱስ ሲኖዶስ ካሉበት አገር ድረስ ሒዶ ኑ ወደ ሀገራችሁ፣ ኑ ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ አብረንም እንሥራ ሲላቸው እምቢ አሻፈረኝ የሚሉበት ምክንያት ገደብ የለሽ የሥልጣን ፍለጋ ካልሆነ ሌላ ምን ነበር? ሐቁ ይህና ይህ ብቻ ነው፤ ስለሆነም ነገሩ በእውነተኛ ሚዛን ሲመዘን እነርሱ እንደሚሉት የሲኖዶስ ጉዳይ ሳይሆን የሥልጣን ፍላጎት በመሆኑ በዚህ ምክንያት አንድ ስንኳ የሚከተላቸው አልተገኘም፤

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው ቤተ ክርስቲያናችን የምትገለገልበትን የአሠራር መዋቅር ለማዛባትና ስያሜውንም ለመለወጥ ሙከራን በማድረግ ላይ የሚገኙት እነዚህ ከአምስት የማይበልጡ ግለሰቦች ለከፍተኛ ደረጃ ባበቃቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ላይ የዓመፅ እጃቸውን በማንሣት ታሪክ ደምሳሽ የሆነ አካሔድ መከተላቸው መላውን ኅብረተ ሰብ ያሳዘነ ቢሆንም ሐቁና እውነቱ ግን ይህ መሆኑን ተረድታችሁ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የምትገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተወህዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በሙሉ ከገንጣይና ከፋፋይ ሥራቸው እንድትርቁ ቤተ ክርስቲያናችን ጥሪዋን ታስተላልፋለች ፤ በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ከዚህ በላይ የተገለፀውን የቃለ ውግዘት ውሳኔ ሰጥቷል።

## <u>ትእዛዝ</u>

ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ውሳኔ በሸኝ ደብዳቤ ሆኖ በሀገርና በመላው ዓለም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አህጉረ ስብከት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲተላለፍ ብለናል ።

ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ